# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ።
# ዋሽንግተን ዲሲ።
# ግንቦት 14 ቀን 1997 ዓ.ም.
# May 22 2005

## <u>አንቀጽ አንድ</u>

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ሀ. ይህ የመተዳደሪያ ደንብ በኅዳር ወር 1988 ዓ.ም. (1994 November) የወጣውን መተዳደሪያ ደንብ ለማሻሻል በ1997 ዓ.ም. ግንቦት ወር (2005 May) ተሻሽሎ የወጣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

2. <u>ትርጓሜ</u>

ሀ. የኢትዮጵያ የተባለበት ቤተ ክርስቲያኑ በልዩ ልዩ ምክንያት ከሀገር ርቀው የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን የሚያሰባስብ በመሆኑና የቤተክርስቲያንዋ መለያ ስም ስለሆነ።

ለ. ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ መባሉ የሃይማኖታችን መጠሪያ ወይም መለያ በመሆኑ

ሐ. ደብረ ምሕረት መባሉ ቅዱስ ሚካኤል የምሕረት መልአክ ተብሎ በመጠራቱ

3. <u>የደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን</u>

ሀ. የደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በዋሽንግተን ዲሲ ሕግና ደንብ መሠረት አትራፊ ያልሆነ በአንቀጽ 501 (ሲ) (3) ላይ በተጠቀሰው ህግ መሠረት የተቋቋመ ሕጋዊ አካል ነው።

ለ. ቤተ ክርስቲያኑ የራሱ የሆነ ሕንፃ እና መሬት ያለው ከዕዳ ነፃ የሆነ ሲሆን አድራሻውም 3010 Earl Place NE, Washington, DC 20018 ነው።

ሐ. የደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ማኅተም ክብ ቅርጽ ያለው በመካከሉ የመስቀል ቅርጽ ያለበትና ዙሪያውን "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን" የሚል ጽሑፍ በአማርኛና በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተቀረጸበት ነው።

መ. ደረቅ ማሕተም (Corporate Seal) ክብ የሆነ ከብረት የተሰራ በእንግሊዘኛ ቋንቋ "Debre Meheret St. Michael Church" በመሀሉ "Corporate Seal 1994 District of Columbia" ተብሎ የተቀረጸበት ነው።

## አንቀጽ ሁለት

4. **ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት።**

ሀ. ኢትዮጵያ ከምትገኘው እናት ቤተክርስቲያን ጋር የእምነት፤ ሥርዓት አምልኮትና ትምሕርተ ሃይማኖት አንድነት አለው።

ለ. ዋና መቀመጫው አዲስ አበባ ኢትዮጵያ የሆነውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የሚቀበልና በአንቀጽ ሁለት ንዑስ አንቀጽ አምስት በፊደል ተራ "ሐ" የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንፈሳዊ አስተዳደር ግንኙነት ያለው።

5. **ሀገረ ስብከትን በተመለከተ**

ሀ. የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ የቅዱስ ሲኖዶስ አባል በመሆናቸው የደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ቡራኬያቸውን ይቀበላል።

ለ. የደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ቦርድ ለደብሩ አስተዳዳሪነት ለመረጠው ካህን የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ መንፈሳዊ መመሪያ ይሰጣሉ።

ሐ. ሀገረ ስብከቱም ሆነ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ የደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር ቦርድ በሚያከናውነው የዕለት ተዕለት ተግባርም ሆነ አስተዳደር ማለትም በሰው፤ በንብረትና በገንዘብ አስተዳደር ጣልቃ አይገቡም።

## አንቀጽ ሦስት

6. **የቤተ ክርስቲያኑ አቋም**

ሀ. የደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አትራፊ ያልሆነ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጥ ነው።

ለ. ከማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ነፃ የሆነ

ሐ. የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ሥልጣነ ክህነት ያለው ካህን

መ. በካህናትና በምዕመናን ቅንጅት የሚመራ የአስተዳደር ቦርድ ያለው

## አንቀጽ አራት

7. **አላማና ተግባር**

ሀ. ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅና አገልግሎቷም የተሟላ እንዲሆን ማድረግ።

ለ. የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮቿ በሐዋርያዊ ተግባራቸው እንዲጠነክሩ ማድረግ።

ሐ. የቤተክርስቲያንን ዶግማ እና ቀኖና መጠበቅና ማስጠበቅ

መ. በኢትዮጵያና በውጭ ሀገር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን ማጠናከርና ቅርሶችዋንም ማስጠበቅ።

ሠ. ተተኪው ትውልድ ሃይማኖቱን፤ ባህሉን፤ ቋንቋውን እንዳይረሳ ማስተማር።

ረ. በኢትዮጵያ የሚገኙትን ገዳማትና አድባራት እንዲሁም የአብነት ትምህርት ቤቶችን መርዳት።

ሰ. ከእናት ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የሚወጣውን ሃይማኖታዊ ውሳኔ በተግባር መተርጐም።

ሸ. ልዩ ልዩ ምግባረ ሠናይ ድርጅቶችን ማቋቋም።

ቀ. የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶችን ማደራጀት።

በ. በአካባቢው ከሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ህብረት መፍጠር።

ተ. የስብከተ ወንጌል አገልግሎትን ማስፋፋት።

ቸ. ምዕመናን ሃይማኖታቸውን ጠንቅቀው እንዲያውቁና በክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር እንዲኖሩ ማድረግ።

## <u>አንቀጽ አምስት</u>

### 8. <u>የቤተ ክርስቲያኑን የመሬት ይዞታና ህንፃ በተመለከተ</u>

ሀ. የደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የመሬት ይዞታና ህንፃው የደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ንብረት ነው።

ለ. የደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያኑን ህንፃም ሆነ መሬት ለመሸጥ ወይም አፍርሶ እንደገና በአዲስ መልክ ለመሥራት በሁለት ሦስተኛው(2/3) የደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አባላት መጽደቅ ያለበት ሲሆን መንበረ ፓትርያርክ፤ ቅዱስ ሲኖዶስ እና የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ እንዲያውቁት ይደረጋል።

## አንቀጽ ስድስት

9. **የአባላት ምዕመናን ሥልጣንና ተግባር**

ሀ. የአስተዳደር ቦርድ መምረጥና መመረጥ

ለ. አስራታቸውንና ወርሃዊ መዋጮ መክፈል።

ሐ. መንፈሳዊ አገልግሎት በነፃ ማግኘት

መ. በዓመት አንድ ግዜ ዓመታዊ ስብሰባ ማድረግ።

ሠ. በአጠቃላይ ስብሰባ ጊዜ አባላቱ ከመቶ ሃምሳ አምስት(55) ከመጡ አጀንዳን ማጽደቅና መወሰን።

ረ. በቂ አባላት ካልተገኙ ለሁለተኛ ግዜ ጥሪ ማድረግ።

ሰ. ለሁለተኛ ግዜ ጥሪ ተደርጎ በቂ አባላት ካልተገኙ ጉባዔው በተገኙት አባላት ተወያይቶ ውሳኔ መስጠት።

## አንቀጽ ሰባት

10. **የአስተዳደር ቦርድ አባላት መለኪያ**

ሀ. የጾታ ልዩነት ሳይደረግ ከካህናትና እንዲሁም ከምዕመናን እድሜያቸው ከሠላሳ በላይ፤ ከሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች እድሜ ከሃያ አምስት በላይ የሆኑ።

ለ. በአባልነት ከተመዘገቡ ከሁለት ዓመት በላይ የሆናቸው

ሐ. በጸባያቸው የተመሰከረላቸው ለሥራ ትጉህ የሆኑና የታመኑ

መ. በማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት በሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ውስጥ የማያገለግሉ።

ሠ. ወርሃዊ ክፍያቸውን ያጠናቀቁ።

ረ. ከተቻለ በንውሳን ኮሚቴ ውስጥ አገልግሎት የሰጡ።

## አንቀጽ ስምንት

11. **የአስተዳደር ቦርድ ሥልጣንና ተግባር**

ሀ. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕግ በሚፈቅደው መሠረት የቤተ ክርስቲያንን እምነትና ሥርዓት መጠበቅና ማስጠበቅ።

ለ. የቤተ ክርስቲያኑን ጠቅላላ ንብረት መጠበቅ

ሐ. ውሎችን መዋዋል።

መ. የቤተ ክርስቲያኑን ገንዘብ በቤተክርስቲያኑ ስም በባንክ ማስቀመጥ።

ሠ. በህግ መቅጠርና ማሰናበት።

ረ. ልዩ ልዩ ንዑሳን ኮሚቴዎችን ማቋቋም።

ሰ. በህግ መክሰስና መከሰስ።

ሸ. የደብሩን አስተዳዳሪና ጸሐፊ መሰየም።

ቀ. እንዳስፈላጊነቱ የክብር የቦርድ አባላትን ይሰይማል።

በ. በዓመቱ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ እንዳስፈላጊነቱ ጠቅላላ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

ተ. የቦርዱን ሊቀመንበር መምረጥና ለሌሎቹም የቦርድ አባላት የሥራ ክፍፍል መስጠት።

ቸ. የደብሩ አስተዳዳሪና ፀሐፊ እንዲሁም የደብሩ ጠቅላላ አገልጋዮች የተሰጣቸውን ኃላፊነት በብቃት የማይወጡ ከሆነ የሥራ መዘዋወር (መቀየር)፡ ሊያደርግ ወይም ሊያሰናብት ይችላል።

ኀ. ይህን መተዳደርያ ደንብ ተግባራዊ ለማድረግ ለሥራ አፈፃጸም የሚረዳውን ልዩ ልዩ ህግጋት ያወጣል።

## አንቀጽ ዘጠኝ

### 12. የቦርድ አባላት ቁጥር (ብዛት)

ሀ. የአስተዳደር ቦርድ አባላት ቁጥራቸው አስራ ሦስት ይሆናል።

ለ. ከካህናት አስተዳዳሪውን ጨምሮ ብዛት አራት ይሆናል።

ሐ. ከምዕመናን ብዛት ስምንት ይሆናል

መ. ከሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች አንድ።

ረ. ከካህናት የሚመረጡትን መርጦ የሚያቀርበው የደብሩ የካህናት ጉባዔ ነው።

ሸ. ከምዕመናን የሚመረጡትን የሚመርጥ ጠቅላላ የምዕመናን ጉባዔ ነው።

ቀ. ከሰንበት ትምህርት ቤት ተወካይ የሚመረጠው በሰንበት ትምህርት ቤት አባላት መራጭነት ነው።

## አንቀጽ አሥር

### 13. የአስተዳደር ቦርድ የአገልግሎት ዘመን

ሀ. የአስተዳደር ቦርድ የአገልግሎት ዘመን አራት ዓመት ይሆናል።

ለ. በጠቅላላ ጉባዔው ቦርዱ በሥራው ከታመነበት ለሁለተኛ ጊዜ ሊመረጡ (ሊያገለግሉ) ይችላሉ።

ሐ. ከሁለት ጊዜ በላይ በተከታታይ ዓመት ማገልገል አይቻልም። ሆኖም በመሀል አራት ዓመት ከአሳለፉ በኋላ በድጋሚ ለመመረጥ ይችላሉ።

መ. የቦርድ አባልነት ጊዜያቸውን የጨረሱ አባላት በንዑሳን ኮሚቴ ውስጥ ሊያገለግሉ ይችላሉ።

ሠ. በአንቀጽ ዘጠኝ ንዑስ አንቀጽ አሥራ ሁለት ፊደል ተራ “ሠ” የተጠቀሱት ሦስት አባላት ቋሚ የቦርድ ክብር አባል ሆነው ያገለግላሉ።

ረ. ከካህናት የሚወከሉ የቦርድ አባላት የሚተካቸው ካህን ከሌለ በተደጋጋሚ ሊመረጡ ይችላሉ።

ሰ. የአስተዳደር ቦርዱ የሥራ ዘመኑን ጨርሶ ሲቀየር አዲስ የተመረጠውን ቦርድ ሥራውን ለማለማመድ የቀድሞው የቦርድ አባላት በየሥራ ዘርፋቸው ከአዲሶቹ የቦርድ አባላት ጋር ለሦስት ወራት ያህል አብረው በመሥራት ሥራውን ያለማምዳሉ።

## አንቀጽ አስራ አንድ

### 14. ከአስተዳደር ቦርድ ስንብት

ሀ. አንድ የቦርድ አባል የሚኖርበትን ሀገር ለቆ ሲሄድ ለጉባዔው በጽሑፍ መልቀቂያ አቅርቦ ይሰናበታል።

ለ. በጤና ማጣት ምክንያት ለመሥራት ካልቻለ ይሰናበታል።

ሐ. አንድ የቦርድ አባል ሃይማኖት የሚያጎድፍ ሥራ ሰርቶ ከተገኘ ወይም ያለ በቂ ምክንያት በተደጋጋሚ ከቦርድ ስብሰባ የሚቀርና ሥራ የሚያጓትት ከሆነ በመጀመርያ በቦርድ አባላት ምክር ይሰጠዋል። የማይሻሻል ወይም የማይመለስ ከሆነ የቦርድ ምልዐተ ጉባዔ በአንድ ድምጽ ከተስማማ ማለትም አሥራ ሁለቱ የቦርድ አባላት ካመኑበት ከቦርድ አባልነት ይሰናበታል። ውሳኔውንም በዓመታዊ አጠቃላይ የምእመናን ጉባዔ ላይ ቦርዱ ያሳውቃል።

መ. የአስተዳደር ቦርድ አባል ሲጎድል በምርጫ ጊዜ ተከታታይ ድምፅ የነበረው ይተካል።

ሠ. ተከታታይ ድምፅ የነበራቸው ካልተገኙ ቦርዱ ከምዕመናኑ መካከል ያገለግላል ተብሎ የታመነበትን ሰው ለጠቅላላው ጉባዔ በማሳወቅ ሊተካ ይችላል።

## አንቀጽ አሥራ ሁለት

### 15. አስመራጭ ኮሚቴ

ሀ. የአስተዳደር ቦርድ አገልግሎት የሥራ ዘመን ከማለቁ በፊት ሦስት ወር ሲቀረው ከአባል ምዕመናን መካከል አምስት አባላት ያሉት የአስመራጭ ኮሚቴ በቦርዱ ይሰየማል።

ለ. የምርጫውን ሥርዓት አስመራጭ ኮሚቴው ለጠቅላላ ጉባዔው ግልፅ በሆነ መንገድ ያዘጋጃል።

ሐ. ምርጫው ከተፈጸመ በኋላ የኮሚቴ ርክክብ ሲደረግም በመገኘት አረካካቢ በመሆን ያገለግላል።

መ. የአስተዳደር ቦርዱ ለአራት ዓመት ብቻ ያገለገለ ከሆነ አስመራጭ ኮሚቴው ቦርዱ ለቤተክርስቲያኑ ጠቃሚ መሆኑን ካመነበት በአንቀጽ አሥር ንዑስ አንቀጽ አሥራ ሦስት በፊደል ተራ “ለ” እንደተጠቀሰው ለጠቅላላ ጉባዔው የቦርዱን ጠቃሚነት አስረድቶ ለቀጣይ አራት ዓመት እንዲመረጡ ማድረግ ይችላል።

## አንቀጽ አሥራ ሦስት

### 16. የቤተ ክርስቲያኑ ገቢ

ሀ. ከምዕመናን በሚሰበሰብ አሥራት
ለ. ከሙዳዬ ምጽዋት
ሐ. ከወርሃዊ መዋጮ
መ. ከሥርዓተ ተክሊል
ሠ. ከስዕለትና ከስጦታ
ረ. ልዩ ልዩ የገቢ ምንጭ በመፍጠር ከሚገኝ ገቢ።

### 17. የቤተ ክርስቲያኑ ወጪ

ሀ. ለካህናት ደመወዝ
ለ. ለመብራት፤ ጋዝ፤ ውኃ፤ ጽዳት፤ የመሳሰሉት
ሐ. ለስልክና የጽሕፈት መሣርያ
መ. ለእንግዳ መቀበያና ለካህናት ሠርከ ሕብስት (ምግብ መግዣ)
ሠ. ለንዋየ ቅድሳትና አልባሳት እንዲሁም የቅርስ እቃዎች

ረ. ለዋስትና (ኢንሹራንስ)
ሰ. ለበጎ አድራጎት

## አንቀጽ አሥራ አራት

### 18. ገንዘብን በተመለከተ

ሀ. የቤተክርስቲያኑ ገንዘብ በሙሉ የሚቀመጠው በቤተ ክርስቲያኑ ስም በተከፈተ የባንክ ሂሳብ (አካውንት) ነው።

ለ. ገንዘቡን በፊርማቸው የሚያንቀሳቅሱ ወይም በቤተ ክርስቲያኑ ስም በተዘጋጀው ቼክ ላይ የመፈረም ሥልጣን ያላቸው
- ❖ የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ካህኑ
- ❖ የቦርዱ ሰብሳቢ
- ❖ የሂሳብ ሹም ይሆናሉ።

ሐ. ከሦስቱ ፈራሚዎች ሁለቱ ከፈረሙበት ገንዘቡ ይንቀሳቀሳል።

መ. የቤተ ክርስቲያኑ ሂሳብ ዓመት ከጀንዋሪ 1 እስከ ዲሴምበር 31 ያለው ዓመት ይሆናል።

## አንቀጽ አሥራ አምስት

### 19. የቦርድ አባላትና የሥራ ክፍፍል

ሀ. የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ከካህናት
ለ. የቦርድ ሊቀ መንበር ከምዕመናን
ሐ. የቤተ ክርስቲያኑ ጸሐፊ ከካህናት
መ. የቦርድ ጸሐፊ ከምዕመናን
ሠ. የሂሳብ ክፍል ከምዕመናን
ረ. የገንዘብ ቤት ከምዕመናንና ከካህናት
ሰ. የቁጥጥር ክፍል ከምዕመናን
ሸ. የንብረት ክፍል ቄሰ ገበዝ ከካህናት (ንዋየ ቅድሳትን በተመለከተ)
ቀ. የሰንበት ትምህርት ቤት ክፍል ከሰንበት ት/ቤት አባላት
በ. የመስተንግዶ ክፍል ከምዕመናን
ተ. የህዝብ ግንኙነት ክፍል ከምዕመናን
ቸ. የበጐ አድራጎት ክፍል ከምዕመናን።
ኀ. የህፃናት ትምህርት ክፍል ከምዕመናን።

## አንቀጽ አሥራ ስድስት

### 20. የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ካህን ሥልጣንና ተግባር

ሀ. ማንኛውንም ምስጢረ ቤተ ክርስቲያን የተመለከቱ ጉዳዮችን ከካህናት የቦርድ አባላት ጋር በመሆን ይመለከታል ይወስናል።

ለ. በቦርድ ስብሰባ ላይ እንደማንኛውም የቦርድ አባል ያለው አንድ ድምፅ ይሆናል።

ሐ. ከቦርድ ሊቀ መንበር ጋር በመሆን በጥምር ፊርማ ማንኛውንም ውሎች ይፈራረማል።

መ. በወጭ የገንዘብ ቼኮች ላይ ከቦርድ ሊቀ መንበር ጋር በጥምር ይፈርማል።

ሠ. የቦርዱ ሰብሳቢ ከሌለ ስብሰባውን ይመራል።

ረ. የወንጌል ትምህርትና የካህናት አገልግሎት በሥርዓት እንዲከናወን ተገቢውን ቁጥጥር ያደርጋል።

ሰ. የቤተ ክርስቲያኑን የዕለት ተዕለት ሥራ ከሚመለከታቸው የቦርድ አባላት ጋር በመሆን ይፈጽማል ያስፈጽማል።

ሸ. በወጪ ደብዳቤዎች ላይ ይፈርማል።

## 21. የአስተዳደር ቦርድ ሊቀ መንበር ሥልጣንና ተግባር

ሀ. የቦርዱን ስብሰባ በሊቀ መንበርነት ይመራል።

ለ. ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሆኑትን ጉዳዮች አይመለከትም።

ሐ. ቤተ ክርስቲያኑን በመወከል ከደብሩ አስተዳዳሪ ካህን ጋር በጥምር ውሎች ይፈራረማል።

መ. በገንዘብ ቼኮች ላይ ከደብሩ አስተዳዳሪ ካህን ጋር በመሆን በጥምር ይፈርማል

ሠ. የቤተ ክርስቲያኑን የዕለት ተዕለት ሥራ በቅርብ ይቆጣጠራል ያስፈጽማል።

ረ. ለቤተ ክርስቲያኑ እድገት የልማት እቅዶችን እየነደፈ ለቦርድ በማቅረብ በሥራ እንዲተረጎም ያደርጋል።

ሰ. ከማንኛውም መንግሥታዊና ህዝባዊ አካላት ጋር ለሚኖረው ግንኙነት ደብሩን ይወክላል።

ሸ. በወጪ ደብዳቤዎች ላይ ይፈርማል።

## 22. የቤተ ክርስቲያኑ ጸሐፊ

ሀ. የቤተ ክርስቲያኑን ማኅተም ይይዛል።

ለ. ማንኛውንም ዓይነት የጽሕፈት መሣርያዎችን ይይዛል።

ሐ. የቤተ ክርስቲያኑን ሰነዶችን ይይዛል።

መ. በቤተ ክርስቲያኑ ቢሮ በመገኘት የዕለት ተዕለት ሥራዎችን ያከናውናል

ሠ. የቦርዱ ጸሐፊ በማይገኝበት ጊዜ የቦርድ ስብሰባ ቃለ ጉባዔ ይይዛል።

ረ. የደብሩ አስተዳዳሪ በሚሰጡት መመሪያ የቤተ ክርስቲያኑን ጉዳዮች ያስፈጽማል። አስተዳዳሪው ከሌሉ እርሳቸውን በመወከል ይሰራል።

## 23. የአስተዳደር ቦርድ ጸሐፊ

ሀ. በቦርድ ስብሰባ ላይ ቃለ ጉባዔ ይይዛል።

ለ. በቦርድ ውሳኔ የተሰጠባቸውን ቃለ ጉባዔዎችንና ልዩ ልዩ ሰነዶችን ይይዛል።

ሐ. ከደብሩ ጸሐፊ ጋር በመተባባር ጠቃሚና ዋና ዋና የሆኑትን ሰነዶች በአግባቡ መያዛቸውንና መኖራቸውን ይቆጣጠራል።

መ. የአስተዳደር ቦርድ ውሳኔዎችን ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ይፈጽማል ያስፈጽማል።

## 24. የገንዘብ ያዥ ሥልጣንና ተግባር

ሀ. የቤተ ክርስቲያኑን ገቢ ገንዘብ በሕጋዊ ደረሰኝ ይሰበስባል።

ለ. በየሳምንቱ እሁድ የሚሰበሰበውን ሙዳዬ ምጽዋት ቆጣሪዎች መድቦ በአግባቡ እንዲሰበሰብ በማድረግ በደረሰኝ ገቢ አድርጎ በቤተ ክርስቲያኑ ስም በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ ያደርጋል።

ሐ. ገቢና ወጪውን በመዝገብ ይይዛል።

መ. በቦርድ ስብሰባ ላይ የሂሳብ አጠቃላይ ሁኔታ ሪፖርት ያቀርባል።

ሠ. የቤተ ክርስቲያኑን የወጪ ቼኮች ይይዛል።

ረ. ወጪዎችን በቼክ አዘጋጅቶ ለፈራሚዎች ያቀርባል።

ሰ. የቤተ ክርስቲያኑ ኦዲተር ለሂሳብ ምርመራ ሰነድ ሲጠይቅ ያቀርባል።

ሸ. ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት ከሂሳብ ክፍልና ኦዲተር ጋር በመተባበር ያቀርባል።

## 25. የሂሳብ ክፍል ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር

ሀ. ገቢውንና ወጪውን በህጋዊ የሂሳብ አያያዝና ደንብ መሠረት በመመዝገብ ይይዛል።

ለ. የባንክ እስቴትመንቶችን እንዲሁም ከገንዘብ ጋር የተያያዙ ሰነዶችን ይቆጣጠራል የሂሳብ መዝገቦችንም ይይዛል።

ሐ. ሂሳቡን በሠንጠረዥ ያዘጋጃል፣ እንዳስፈላጊነቱ ለቦርዱ ሪፖርት ያቀርባል።

መ. የደብሩ አስተዳዳሪ ወይንም የቦርዱ ሊቀ መንበር በማይገኙበት ጊዜ በወጪ ቼኮች ላይ በጥምር ይፈርማል።

ሠ. በጀት በሚደለደልበት ጊዜ በቂ ገንዘብ መኖሩን ያረጋግጣል።

## 26. የቁጥጥር ክፍል ሥልጣንና ተግባር

ሀ. ገቢውንና ወጪውን ይቆጣጠራል፤ ገንዘብ በባንክ መቀመጡን ያረጋግጣል።

ለ. ገቢና ወጪ የተደረገባቸውን ደረሰኞች ህጋዊ መሆናቸውን ይቆጣጠራል።

ሐ. ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት ያዘጋጃል።

መ. በየወሩ ያሉትን ወጪዎች በሰዓታቸው መከፈላቸውን ይቆጣጠራል።

## 27. የንብረት ክፍል

ሀ. ቋሚና አላቃ የሆኑ ንብረቶችን ይጠብቃል፤በመዝገብ ይይዛል።

ለ. ካህን ከሆነ ቄሰ ገበዝ ተብሎ ከታቦተ ህጉ ጀምሮ ያሉትን ማንኛውንም ንዋየ ቅድሳት ይጠብቃል ያስጠብቃል።

## 28. የህዝብ ግንኙነት ክፍል

ሀ. ምዕመናን ከቤተ ክርስቲያን ሳይመጡ ከሰነበቱ ተከታትሎ የቀሩበትን ምክንያት ማወቅና መፍትሔ መፈለግ።

ለ. በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ የሚለጠፉ ጽሑፎችን መቆጣጠርና ኃላፊነት መውሰድ።

ሐ. ለምዕመናኑ እንዲደርሱ የሚደረጉ ጽሁፎችን ማሰራጨት።

መ. ምዕመናኑ የአባልነት ቅጽ እንዲሞሉ ማስተባበር።

ሠ. ከምዕመናን የሚመጡ ጥያቄዎችን ለቤተ ክርስቲያኑ አስተዳደር በማቅረብ መልስ እንዲያገኙ ማድረግ።

## 29. የመስተንግዶ ክፍል

ሀ. ለበዓል ከሩቅም ከቅርብም የሚመጡትን እንግዶች መቀበል።

ለ. በንግሥ በዓል ለእንግዶችና ለህዝቡ የምግብ ዝግጅት ማድረግና ማስተናገድ።

ሐ. በየሳምንቱ እሁድ ከቅዳሴ በኋላ ለምዕመናኑ ቡናና ሻይ እንዲስተናገዱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት።

## 30. የሰንበት ትምህርት ቤት

ሀ. የሰንበት ትምህርት ቤቱ የቤተ ክርስቲያኑ አካል እንደመሆኑ መጠን አንድ ተወካይ በአስተዳደር ቦርድ ውስጥ ይኖረዋል።

ለ. የነገ ቤተ ክርስቲያን ተረካቢዎች በመሆናቸው የሃይማኖት ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ።

ሐ. በየሳምንቱ እሁድ ለምዕመናኑ በቤተክርስቲያን ተገኝተው መዝሙር ማቅረብ።

መ. ከቤተ ክርስቲያኑ አስተዳደር የሚሰጠውን መመሪያ መፈጸምና ማስፈጸም።

ሠ. መንፈሳዊ ድራማዎችንና ዝግጅቶችን ለምዕመናን ማቅረብ

ረ. በአካባቢው ከሚገኙ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማኅበራት ጋር ሕብረት መፍጠር።

## 31. የህፃናት ክፍል

ሀ. ህፃናት ሃይማኖታቸውን ባህላቸውንና ቋንቋቸውን እንዲያውቁ ማስተማር

ለ. በየሳምንቱ እሁድ እድሜያቸው አነስተኛ የሆኑትን በመሰብሰብ በቅዳሴ ጊዜ እነርሱን በማስተማር የቅዱስ ቁርባን ሰዓት ሲደርስ አሰልፎ ማምጣት።

ሐ. ታዳጊ ሕፃናት በቤተ ክርስቲያን ተኰትኩተው እንዲያድጉና የነገይቱንቤተ ክርስቲያን ተረካቢዎች እንዲሆኑ ጥረት ማድረግ።

# አንቀጽ አሥራ ሰባት

## 32. መተዳደሪያ ደንቡን በተመለከተ

ሀ. ይህ የመተዳደሪያ ደንብ በአሥራ ሰባት አንቀጽ፣ በሠላሳ ሁለት ንዑስ አንቀጽና፣ በመቶ ሰባ ስድስት ፊደል ተራ ይከፈላል።

ለ. ይህ ደንብ በአስተዳደር ቦርድ አባላት ታምኖበት ለሁለተኛ ጊዜ ተሻሽሎ የወጣ በመሆኑ የቦርድ አባላት ከፈረሙበት ጊዜ ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል።

ሐ. ደንቡን ማሻሻል ሲያስፈልግ የአስተዳደር ቦርዱ አጥንቶ ለጠቅላላው ጉባዔ በማቅረብ በ2/3ተኛ አባላት ድምፅ ሊሻሻል ወይም ሊቀየር ይችላል።

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ።

# ዋሽንግተን ዲሲ።

# ግንቦት 14 ቀን 1997

# May 22 2005

*ይህ የመተዳደሪያ ደንብ*
*በአሥራ ሰባት አንቀጽ*
*በሠላሳ ሁለት ንዑስ አንቀጽና*
*በመቶ ሰባ ስድስት ፊደል ተራ የተከፈለ ነው።*